# <u>መቶ አለቃ መሥፍን ክብረት</u>

*ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ/ም ሐረር፣ ኢትዮጵያ*

*መጋቢት ፲፭ ቀን ፪ሺህ ፲፮ ዓ/ም*


*አሌክዛንድሪያ፣ ቨርጂኒያ አሜሪካ*



# <u>Lt. Mesfin Kebret</u>

January 20, 1952, Ethiopia - March 24, 2024, Alex. VA. USA

# የመቶ-አለቃ መሥፍን ክብረት




*ጥር ፲፮ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ/ም -  መጋቢት ፲፫ ቀን ፪ ሺህ ፲፪ ዓ/ም*

# የመቶ-አለቃ መሥፍን ክብረት አጭር የሕይዎት ታሪክ፣

መቶ-አለቃ ሙፍን ክብረት ከአባታቸው ከአቶ ለማ ወልደየስ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ አሰለፈች ክብረት ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ/ም ሐርር ልዩ ስሙ መድፍ መተኮሻ ሠፈር ተወለዱ።

ህጻን መሥፍን ሁለት-ዓመት-ተኩል ሲሆነው መድኀኒዓለም ቤተ-ክርሲቲያን ትምርቱን በመጀመር አንደኛ ክፍልን እንዳጠናቀቀ ቤተሰቦቹ በሥራ ምክንያት ወደ ዓለማያ /ሀረማያ/ በመዛወራቸው በጊዜው እስከ-ሦስተኛ ክፍል ብቻ ያስተምር በነበረው ስዊዲሽ ሚሽን ሁለተኛ እና ሦስተኛ ክፍሎችን ተማረ። በመቀጠልም ሐረር ልዑል ራስ መኮንን ት/ቤት በመግባት ከአራተኛ እስከ አሥራ-አንደኛ ክፍል ተምሮ በአገሪቱ ካሉ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከፍተኛ ውጤት ያላቸውን እና የጤናም የአካላዊ ብቃትም ያላቸውን እየተቀበለ በእጩ-መኮንነት ያሰለጥን በነበረው ታዋቂው የቀ.ኃ.ሥ. ጦር አካደሚ በተቋቋመው አዲስ ወታደራዊ መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚሰጠውን የቀለም እና መሠረታዊ ወታደራዊ ሥልጠና በፍተኛ ውጤት አጠናቋል። መስናዶ ት/ቤቱ ካስመረቃቸው የመጀምሪያ ዙር ተማሪዎች አንዱ ሆኖ የጦር አካደሚውን በ፲፫ኛ ምድብ እጩ-መኮንንነት የሚሰጠውን የሦስት ዓመታት ሥልጠና በማጠናቀቅ በምክትል የመቶ-አለቃ ማዕረግ ተመርቋል።



መቶ-አለቃ መሥፍን ዝነኛው የኢትዮጵያ የአየር-ወለድ፣ በራሪ ነብር ክፍል አባል በመሆን በኤርትራ እና በሌሎች ክፍሎች የተጣለባቸውን ውታደራዊ ግዳጆች እና ኃላፊነቶች በከፍተኛ ብቃት ተወጥተዋል።

ከተጣሉባቸው ኃላፊነቶች ውስጥ አንደኛው ደርግ ከዙፋናቸው አውርዶ ለእስር የዳርጋቸውን አፄ ኃይለ-ሥላሴን መጠበቅ ነበር። ይኸ ኃላፊነት መኮንኑ የአፄ ኃይለ-ሥላሴን ሁኔታ በጣም በቅርበት ለመከታተል፣ ብዙ ነገሮችን ለመረዳት እና ለመታዘብ አስችሏቸዋል።

በወታደራዊ ሕይዎታቸውም ሆነ ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከማንኛውም ዓይነት ጭቆና እና በደል ተላቅቆ የፍትኃዊ ሥርዓት ባለቤት እንዲሆን እና የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት ተከብሮ እንዲቀጥል በተሣተፉበት የትግል ሕይዎታቸው ያሣለፉትን፣ የታዘቡትን እና የሚያውቁትን በተመለከተ መጽሐፍ እንዲጽፉ በቅርብ ከሚያውቋቸው ጓደኞቻቸው እና ወዳጆቻቸው ይቀርብላቸው የነበረውን ያላሰለሰ ጉትጎታ በመጨረሻ ተቀብለው በማዘጋጀት ላይ ነበሩ።

ጽሑፋቸው ከአስተዳደጋቸው ጀምሮ በወታደራዊ ሕይዎታቸው ስላሳለፋት ተመክሮ፣ በጣም ከሚወዱት አየር-ወለድ ጦር ለምን መውጣት እንደተገደዱ እና ወደ-ትግል እንደገቡ፣ ወዘተ… የሚዘረዝር በመሆኑ፣ በአንድ ወቅት በአጭር-በአጭሩ በተከታታይ ለሕዝብ ለማቅረብ አስበው ነበር። በሕይዎት እያሉ ለሕትመት አለመብቃቱ ቢያጸጽትም፣ ፍላታጎታቸው ግን ተፈጻሚ ይሆናል።






መቶ-አለቃ መሥፍንን ከደርግ ሥርዓት አመራር ጋር ካለያያቸው እና ከልብ ከሚውዱት ወታደራዊ ሙያ ወጥተው ወደ-ትግል እንዲግቡ ካደረጓቸው ምክንያቶች አንዱ ወታደሩ የአገርን አንድነት በማስከበሩ ዋና ተልዕኮው ላይ ሊሠማራ እንጅ ጥንታዊት እና ታሪካዊት የሆነች ኢትዮጵያችንን አዲስ ነፃ እንደወጡ አገሮች በመከላከያ ስም የጥቂት አምባ-ገነኖች መጫዎቻ መሆን የለባትም፣ ለዴክርሲያዊ ሥርዓት ምሥረታም እንቅፋት ነው የሚል

ሲሆን፤ ሁለተኛው አገራቸውን በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት ያገለገሉ የመንግሥት ባሉሥልጣናትን እና የኢትዮጵያ ጦር አዛዦችን ያለ-አንዳች የፍርድ ሂደት በጅምላ መጨፍጭፋቸው ኢትዮጵያን ወደ-ተሻለ ሥርዓት የሚወስድ ሣይሆን እጅግ ወደ-ኋላ የሚያቀር አደገኛ ጨርሶ ኃላፊነት የጎደለው አካሄድ እንደሆነ በመገንዘባቸው እና በማመናቸው መሆኑን ይናገሩ ነበር። ይኽንም በጽሑፋቸው ይገልጻሉ።


ግፍን የመጸየፍ እና ለፍትኅ ልዩ ሥፍራ የሚሰጡት የነቁ አገር-ወዳዱ መቶ-አለቃ መሥፍን የአየር ወለድ ጦር ከሌሎች የጦር ክፍሎች ጋር በመተባበር የመንግሥት ለውጥ እንዲደረግ በነበረው የውስጥ እንቅስቃሴ ግንባር-ቀደም ሆነው ሲያስተባብሩ ከነበሩት አንዱ ነበሩ።

ያ የለውጥ ጥረት ሳይሳካ ሲቀር ለእሣቸውም ሆነ ለሌሎች ጓደኞቻቸው የነበራቸው ምርጫ አንድም ስደት ወይም በአድር-ባይነት የማያኑበትን መንግሥት ማገልገል አለበለዚያ ትግላቸውን በሌላ መልክ መቀጠል ነበር። ምርጫቸው ትግሉን በመቀጠሉ ላይ እንዲሆን ወስነው ኢሕአሠን በመቀላቀል በትግራይ እና በጎንደር ክፍለ-አገሮች በአሠልጣኝነት እና በወታደራ የኃይል መሪነት ታግለዋል።

በድርጅቱ ውስጥ ያልተጠበቀ ችግር ሲፈጠር፣ ጨርሶ ይሆናል ብለው ባልገመቱት ሁኔታ ከአገር መውጣት ግዴታ ሆኖባቸው ለአጭር ጊዜ ሱዳን ቆይተዋል። በጊዜው የአሜሪካ መንግሥት የፖለቲካ ስደተኞችን ለመቀበል

የከፈተውን ዕድል ተጠቅመው ወደ አሜሪካ በመምጣት እስከ ዕለተ-እረፍታቸው ድረስ የአሜሪካ ኗሪ ነበሩ።








ኑሯቸውን በአሜሪካ ካደረጉም በኋላ በአገራቸው ጉዳይ ከመሣተፍ ቦዝነው አያውቁም። በአገር-ወዳድ፣ በኢዴኃቅ፣ በኅብረት፣ በኅብረሕዝብ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በልዩ-ልዩ ደረጃዎች ተሣትፈዋል።የቀድሞ ሠራዊት አባላት ማኅበር የአመራር አባል በመሆን አገልግለዋል።



መቶ-አለቃ መሥፍን ቀደም-ሲል ከሚኖሩበት ሣንፍራንሲስኮ ወደ-ቨርጂኒያ ከመጡ በኋላ ከባለቤታቸው ከወ//ሮ መቅደስ አስናቀ ጋር ትዳር መሥርተው የሁለት ልጆችን፣ በአካል እና ዳግምን አፍርተዋል።







አገር-ወዳዱ መቶ-አለቃ መሥፍን ክብረት ሲበዛ ጨዋ፣ ከስሜታዊነት የራቁ፣ በጣም የተረጋጉ፣ ርኅሩኅ፣ ለጋስ እና ዝምተኛ ኢትዮጵያዊ መኮንን ነበሩ።







ታጋይ መቶ-አለቃ መሥፍን/ዱባለ ክብረት ከቅርብ ጊዜ ወዲኽ ባደረባቸው የጤና መታውክ ምክንያት በሕክምና ላይ እያሉ መጋቢት ፲፰ ቀን ፪ ሺህ ፲፮ ዓ/ም ከዚህ ዓለም ተለይተዋል።

ፈጣሪ ነፍሳቸውን በአፀደ-ገነት ያሣርፍ፤ ለውድ ባለቤታቸው፣ ለልጆቻቸው፣ ለዘመድ-አዝማድ፣ ለረዥም ጊዜ የትግል ጓደኞቻቸው እና ጓዶቻቸው መጽናናት እና ብርታትን ይስጥልን።

***መሥፍኔ፣ የትዕግስት፣ የጽናት፣ የእርጋታ እና የትኅትና ውሃ-ልክ!!***



*‘መልካሙን ገድል ታግያለሁ፣ ሩጫየን ጨርሻለሁ፣ ሐይማኖቴን ጠብቄአለሁ።’* ***፪ ጢሞ. ም/ፍ ፬ ቁ.፯***